# በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን


**ÄTHIOPISCH-ORTHODOXE KIRCHE IN DEUTSCHLAND**

**Ueckeratherstr. 2, D-50739 Koeln**

**Tel/ Fax: 0221/ 599 2623**

E-mail: aeokd@gmx.de

www.aethiopisch-orthodoxe-kirche-deutschland.de

Bankverbindung:
Commerzbank
Kto. 1121 383
BLZ 370 40044


*የትንሣኤ መልእክት* ሚያዝያ ፳፻፬ ዓ. ም./April 2012

## *„በአማን ተንሥአ እግዚእነ“ ጌታችን በእውነት ተነሥቷል*

*የተወደዳችሁ አባቶች መነኮሳትና ካህናት፣ ወንድሞች ዲያቆናት*
*ውድ መዘምራንና መዘምራት፣ የተወደዳችሁ ምእመናንና ምእመናት!*

ለሰው ልጆች ሁሉ ቤዛ ለመሆን በመስቀል ተሰቅሎ የሞተው፣ በማሕየዊ ሞቱ ሞትን አሸንፎ፣ በቅድስት ትንሣኤው የመቃብርን አስፈሪ ግርማ ደምስሶ በድል አድራጊነት የተነሣው የሁላችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መዋዕለ ጾሙን በሰላም አስፈጽሞ፣ ጾመ ልጓሙን ፈቶ እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ በማለት በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና በራሴም ስም በቅድሚያ ልባዊ ምኞቴን ልገልጽ እወዳለሁ።

የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም ጎልጎታ በተባለው ቦታ መግነዝ ፍቱልኝ፣ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ሞትን በሞቱ አሸንፎ፣ የመቃብርን አስፈሪ ግርማ በትንሣኤው ደምስሶ በድል አድራጊነት ተነሣ። ክብር ምስጋና ይግባውና በእርሱ ትንሣኤ የእኛን ትንሣኤ አረጋገጠልን። በመሆኑም ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከኃሣር ወደ ክብር፣ ከመርገም ወደ በረከት፣ ከሲኦል ወደ ገነት፣ ከገሀነመ እሳት ወደ መንግሥተ ሰማያት ተሸጋገርን። በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶሰ ያመነ የዘለዓለም ሕይወት አልው ተብሏልና፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የዘለዓለም ሕይወት፣ የሕይወት ራስ፣ ትንሣኤ፣ ብርሃንና ሕይወት እንደሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት፣ በሐዋርያት ትምህርትና በሊቃውንት ስብከት ተረጋግጧል። ዘለዓለማዊ የሆነችውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ በቅድሚያ በጨለማ ከተመሰለው፣ በሞት ጥላ ሥር ካለው ከኃጢአት ሥራችን፣ ከክፉ ተግባራችን ልንላቀቅ ያስፈልጋል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሁልጊዜም መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሲል በቀራንዮ በመልዕልተ መሰቀል መሰቀሉን፣ ስለእኛም ነፍሱን አሳልፎ መስጠቱን ብቻ ሳይሆን ሞትን አሸንፎ መነሣቱን፣ ድል አድራጊነቱንና ሕያው መሆኑን ታስተምረናለች። በምድራዊ ኑሯችን በቅዱስ ቃሉ ከተመላለስን፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከታደስን ሙታን ሕያዋን የሚሆኑበት፣ ሬሳዎች የሚነሡበት ቀን ይመጣልና ደስ ይበለን።<< ትንሣኤህን ለአመንን ለእኛ ብርሃንህን ግለጽልን >> እያልን እንዘምር። በብርሃኑም እንመላለስ።

*ውድ ወገኖቼ፣*

የፍቅር ባለቤት፣ የሰላም ንጉሥ ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ለውድ አገራችን ለኢትዮጵያ፣ ለምንኖርበት አገር ለጀርመንና ለዓለም ሁሉ ሰላምን፣ ፍቅርንና አንድነትን፣ ለቤተ ክርስቲያን አባቶች መቻቻልንና ማስተዋልን፣ ለተሰደዱ መረጋጋትን፣ ላዘኑና ለተከዙ መጽናናትን፣ በሰንሰለት ታሥረው በእስር ቤት ላሉት መፈታትን፣ ለተራቡት የዕለት ምግብን፡ ለተራቆቱት የዓመት ልብስን፣ ለታመሙት ጤንነትን፣ ለሙታን ዘለዓለማዊ ዕረፍትን ያድልልን። የተቀደሰም ወርኃ ትንሣኤ ይሁንልን። አሜን!

*ሊቀ ካህናት ዶ/ር መርዓዊ ተበጀ*

(ከዚህ ቀጥሎ በዋልድባ ገዳማት ዙሪያ ለመንበረ ፓትርያርክ የተጻፈውን ግልጽ ደብዳቤ እንድታውቁት ተልኳል፤)



*ግልጽ ደብዳቤ*

ለብፁዕ አቡነ ፊልጶስ፤
የኢሊባቦርና የጋምቤላ አህጉረ ስበከት ሊቀ ጳጳስና የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራአስኪያጅ፤

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

ብፁዕ አባታችን!

በቅድሚያ የብፁዕነትዎ መንፈሳዊ ቡራኬ እንዲደርሰን እንመኛለን፤

*ጉዳዩ፡-በዋልድባ ገዳምና በአካባቢው ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ያለንን ስጋት ያመለክታል።*

እኛ በጀርመን ሀገር የምንገኝ ማኅበረ ካህናትና ማኅበረ ምእመናን በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች ከስማነው በመነሣት ሳይሆን ከቤተ ክህነትና ከመንግሥት ከተነገረው በመነሣት ካልጠፋ ቦታ *በልማት ስም አብያተ ክርስቲያናት ይነሣሉ የሚለውን ውሳኔና* *በሰላም ያረፈ የወገኖቻችን አጽም* ከቦታው እንዲነሣ መደረጉ የኅሊና ዕረፍት ሊሰጠን አልቻለም። በአሰቦትና በዝቋላ ገዳማት ደን ላይ በደረሰው ቃጠሎ ተጠያቂ አለመኖሩ ደግሞ እጅግ አሳዝኖናል።

*ብፁዕ አባታችን!*

*እንደዚህ ባለ ዐቢይ ጉዳይ ላይ በገዳሙ የመነኩሱ ሊቃነ ጳጳሳት ካሉበት ከቅዱስ ሲኖዶስና ከጠ/ቤተ ክህነት የተሠወረ ይኖራል ብለን ስለማናምን ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን ከማቅረብ ተቆጠበን በእናት ቤተ ክርስቲያንና በተከታዮቿ ህልውና ላይ ያንዣበበ ደመና መኖሩን ግን በቤተ ክርስቲያን ልጅነታችን ልንገልጽ እንወዳለን። የአባቶች ዝምታም አስደምሞናል። እስከ መቼ ድረስ ?!*

ከዛሬ ፸፮ /76/ ዓመት በፊት የሊማሊሞን ገደል የደፈረ የኢጣልያ ግብረ ኃይልና ጦር በባጠገቡ ሲያልፍ ያልደፈረው ገዳማችን ሊደፈር አይገባውም በማለት አቤት እንላለን፤፤ *የገዳማውያኑና የመናንያኑ ጩኸታቸው ጩኸታችን፤ ስጋታቸው ስጋታችን፤ ጭንቀታቸው ጭንቀታችን፤ ኃዘናቸው ኃዘናችን ነው።*

*መንግሥት የፈረደባቸው በገዳመ ዋሊ አካባቢ ያሉ፤ እጅግ መራራ ዘመናትን አሳልፈው ከዘመናችን የደረሱ አብያተ ክርስቲያናት ከፈረሱ፤ " መሐሉ ገነት ጻሩ እሳት " ይሁን ተብሎ የተገደመው ገዳም ጻር ደንበሩ ሲፈርስ መሐሉ መደፈሩ አይቀርምና* *ይግባኝ ለእግዚአብሔርና ለዓለም ሕዝብ* ለማለት የተዘጋጀን መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፤ የሚሰጠን ማብራሪያ ካለም ከልብ እናመሰግናለን

የብፁዕነትዎ ቡራኬ አይለየን።

*መ ል ካ ም የ ት ን ሣ ኤ በ ዓ ል*

ሊቀ ካህናት ዶ/ር መርዓዊ ተበጀ

ግልባጭ፤-

ለመንበረ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት
ለመንግሥት አካላት
ለሚመለከተው ሁሉ
ለሕዝብ የመገናኛ ተቋማት